Ministry of justice

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 18
ADDIS ABABA 11th February, 2011

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፯፻፩/፪ሺ፫

ለጅጅጋ-ደገሐቡር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፭ሺ፯፻፴፰

Proclamation No. 701/2011

Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Rural Electrification Project in Jijiga-Degahabur Ratification Proclamation Page 5738

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፩/፪ሺ፫

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጅጅጋ-ደገሐቡር አካባቢዎች ገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፲ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር /አሥር ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፬ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ባካሔደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለጅጅጋ-ደገሐቡር አካባቢዎች የገጠር ኤሌክትሪክ ሥርጭት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፩/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 701/2011.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

**WHEREAS** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 10,000,000 USD (ten million United States Dollars) for financing the Rural Electrification Project in Jijiga-Degahabur, was signed in Addis Ababa, on the 4th day of March 2010;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 11th day of January, 2011;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Rural Electrification Project in Jijiga - Degahabur Ratification Proclamation No. 701 /2011".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Ministry of justice

፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፬ ቀን ፪ሺ፲ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር /አሥር ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed on the 4th day of March 2010 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 10,000,000 USD (ten million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date.**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 11th day of February, 2011

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት